የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፳፫
አዲስ አበባ — ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

2nd Year No. 23
ADDIS ABABA – 14th May, 1996

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፹፰ ዓ·ም·
ለብሔራዊ የዘር ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ...................................... ገጽ ፻፸፪

## CONTENTS

Proclamation No. 35/1996
International Development Association Loan Agreement for Financing the National Seed Project Ratification Proclamation .................................... Page 172

## አዋጅ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፹፰

### በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

ለብሔራዊ የዘር ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ የሚውል መጠኑ ኤስ·ዲ·አር· 15,200,000 (አሥራ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር·) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመ በመሆኑ ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው ስለሆነ ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለብሔራዊ የዘር ፕሮጀክት ማስፈጸሚያ ከዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር ብድር ለማግኘት የተፈረመውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፴፭/፲፱፻፹፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

## PROCLAMATION NO. 35/1996

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 15,200,000 SDR (fifteen million two hundred thousand Special Drawing Rights) for financing the National Seed Project, was signed in Washington D.C., on the 29th day of September, 1995;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 14th day of May, 1996;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement for Financing the National Seed Project Ratification Proclamation No. 35/1996."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price } 1·20

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ "የብድር ስምምነት" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም አቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ·ኤ·አ· ሴፕቴምበር ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፭ በዋሽንግተን ዲ·ሲ· የተፈረመው ቁጥር ፪ሺህ ፯፻፵፩ ኢ.ት (እንደተሻሻለ) የብድር ስምምነት ነው ።

፫· <u>የገንዘብ ሚኒስትሩ ሥልጣን</u>

የገንዘብ ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፲፭ ሚሊዮን ፪፻ ሺህ (አሥራ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሺህ ኤስ·ዲ·አር·) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፬· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፮ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2. *Definition*

In this Proclamation "Loan Agreement" means the Loan Agreement No. 2741 ET (as amended) signed in Washington D.C., on the 29th day of September, 1995 between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association.

3. *Power of the Minister of Finance*

The Minister of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 15,200,000 SDR (fifteen million two hundred thousand Special Drawing Rights) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 14th day of May, 1996.

Done at Addis Ababa, this 14th day of May, 1996.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE